# የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ (የአድሚኒስትራሲዮን) ፡ ውሎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡

ክሬኔ ፡ ዳቪድ ።*

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ አርዕስት ፡ እራሱ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ይመስል ፡ ይሆናል ። ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ የሚለውን ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳብ ፡ አንዳንድ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅቶች ፡ (ሲስተምስ) ፡ ሲጠቀሙበት ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ አይጠቀሙ በትም ። አንዳንዶቹ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅቶች ፡ በዚህ ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳብ ፡ የሚጠቀሙ በት ፡ ምክንያት ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎችን ፡ ከጠቅላላው ፡ የፍ ትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ አውጥቶ ፡ በልዩ ፡ ያስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ ሥር ፡ ለማድረግ ፡ ሲባል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥር ፡ የማይጨመሩት ።

በዚህ ፡ ረገድ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታውጆ ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ፭ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ (ስለልዩ ፡ ውሎች) ፡ ስላስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ የሚናገሩ ፡ ፻፸፮ ፡ ቍጥሮች ፡ (ከቍ ፡ ፫ሺ፩፻፴፩—፫ሺ፫፻፮) ፡ የያዘውን ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ን ፡ ይጨምራል ። በዚሁ ፡ ባ፭ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከአንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ የሚመጡት ፡ መብቶች ፡ ማስተላለፍን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ (አንቀጽ ፡ ፲፭) ፡ የሥራዎች ፡ አገልግሎት ፡ መስጠትን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ (አንቀጽ ፡ ፲፮) ፡ የዕቃ ፡ ጥበቃን ፡ በዕቃ ፡ መገልገልን ፡ ወይም ፡ በዕቃ ፡ መጠቀምን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ (አንቀጽ ፡ ፲፯) ፡ እና ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ የሚናገሩት ፡ አንቀጾች ፡ ናቸው ። ከአንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ ለጥቆ ፡ የሚመጣውና ፡ የመጨረሻው ፡ አንቀጽ ፡ ስለ ፡ ግልግልና ፡ ስለ ፡ ስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ ውል ፡ የሚናገረው ፡ ነው ።

እንዲህ ፡ ያለ ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተደረገ ? የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ ረቂቅ ፡ እንዳዘጋጅ ፡ አደራ ፡ የተጣለብኝ ፡ እኔ ፡ ስለ ፡ ነበርኩ ፡ ይህንን ፡ ጥያቄ ፡ ለመመለስ ፡ የተመቸ ፡ ቦታ ፡ ያለሁት ፡ እኔው ፡ ነኝ ። ፈረንሳዊ ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ እንደመሆኔ ፡ መጠን ፡ ለኔ ፡ እን ደሚመስለኝ ፡ ጠቅላላውን ፡ ሕግ ፡ በምንከፋፍልበት ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥት ፡ ሕግ ፡ ከግል ፡ ሕግ ፡ በተለይም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ካስተዳደር ፡ ሕግ ፡ መለየቱ ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። የመንግሥቱ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የሕዝቡን ፡ ጥቅም ፡ እንዲጠብቁና ፡ እንዲያከባክቡ ፡ አደራ ፡ ተጥሎባቸዋል ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ቢታ ወቅላቸውም ፡ ባይታወቅላቸውም ፡ እነዚህ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ከግል ፡ ኗሪዎች ፡

(ከተራ ፡ ሰዎች) ፡ በእርግጥ ፡ የተለየ ፡ አቋም ፡ አላቸው ። የመንግሥት ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ የተዋዋሏቸው ፡ ውሎች ፡ ያስተዳደር ፡ መምሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ የሚያሰኝ ፡ ልዩ ፡ ጠባይ ፡ ሲኖራቸው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ በተለዩ ፡ ደንቦች ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ማድረግ ፡ ከትክክለኛ ፡ ፍትሕ ፡ ጋር ፡ የሚስማማ ፡ ነው ።

ሁሉም ፡ የሕግ ፡ ቅንጅቶች ፡ (ሲስተምስ) ፡ እነዚህን ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ፡ ማውጣት ፡ ነበረባቸው ። የተለያዩ ፡ የሕግ ፡ ቅንጅቶች ፡ ባወጧቸው ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ያንዱ ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ፡ የሌላውን ፡ ያህል ፡ ጐልተው ፡ አለመታየታቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አስተዳደር ፡ መምሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ የሚናገሩ ፡ የተለዩ ፡ ጽሑፎች ፡ ወይም ፡ እነዚህን ፡ ውሎች ፡ የሚነካ ፡ ክርክር ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ የመዳኘት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ የተለዩ ፡ ያስተዳደር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለሌሉ ፡ ነው ።

የሕግ ፡ መሰናዶ ፡ ሲደረግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነበር ።

የተለዩ ፡ ያስተዳደር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንዳሁኑ ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ አልነበሩም ። በተጨማሪም ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የተጻፉ ፡ ጽሑፎች ፡ ስላልነበሩ ፡ እንደ ፡ ምዕራባውያን ፡ ሕጐች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ በኢትዮጵያ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ለመተማመን ፡ አይቻልም ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ያስተዳደር ፡ መምሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ የሚለውን ፡ ጽንስ ፡ ሐሳብ ፡ እንጠቀምበት ፡ ወይስ ፡ እንጠቀምበት ፡ የሚለው፡ ምርጫ ፡ ክፍት ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ምርጫ ፡ መኖሩንና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥም ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ በመመልከት ፡ ላስተዳደር ፡ መምሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ የሚውሉ ፡ ደንቦች ፡ ለመምሪያ ፡ ያህል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይደረጉ ፡ ወይም ፡ መግባታቸው ፡ ይቅርና ፡ ትልቅ ፡ ያልተረጋጋና ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ሁኔታ ፡ ይፈጠር ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ አድሮብኝ ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ሐሳብ ፡ መፈጸሙ ፡ የማይቀር ፡ መስሎ ፡ ታየኝ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አቋም ፡ እነዚህ ፡ ውሎች ፡ በተለዩ ፡ ደንቦች ፡ እንዳይተዳደሩ ፡ አያግድም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ፡ በቀላሉ ፡ በሕግ ፡ አይወሰኑም ።

በዚህ ፡ አካባቢ ፡ ያለውን ፡ ሁኔታ ፡ አብራርቶ ፡ መግለጽ ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ነበር ። የመንግሥትና ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተግባር ፡ እየጨመረ ፡ በመሄዱ ፡ ባለፉት ፡ ቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በሁሉም ፡ አገሮች ፡ የአስተዳደር ፡ መምሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነዋል ። ይህ ፡ በፈረንሳይ ፡ በእንግሊዝ ፡ በአሜሪካን ፡ አገር ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ "በሶሺያሊስት" ፡ ሀገሮችና ፡ "ሊብራል" ፡ ኢኮኖሚ ፡ ባላቸው ፡ ሀገሮች ፡ መካከል ፡ በሚገኙት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በቀሩት ፡ ሀገሮች ፡ የበለጠ ፡ እውነት ፡ ይኖረዋል ። የነዚህ ፡ ሀገሮች ፡ የኢኮኖሚ ፡ ዕድገት ፡ መረዳት ፡ ያለበት ፡ ከግል ፡ ሥራዎች ፡ የሚገኘውን ፡ ያህል ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ ከሕዝብና ፡ ሕዝብ ፡ ነክ ፡ ከሆኑ ፡ ሥራዎች ፡ ነው ። በ"ሊብራል" ፡ ኢኮኖሚ ፡ አቋም ፡ እንኳን ፡ የግል ፡ ሥራዎች ፡ እንዲነቃቁና ፡ ሥራቸውን ፡ እንዲያከናውኑ ፡ ለማድረግ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ባስተዳደር ፡ መምሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ መጠቀም ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆናል ።

ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ካፒታል ፡ በሚያጥርበት ፡ ሀገሮች ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ በኢትዮጵያም ፡ መኖሩ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ያገሪቱ ፡ ዕድገት ፡ መረዳት ፡ ያለ

ቤት ፡ ሳገር ፡ ውስጥና ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ኮንሴሲዮኖች ፡ በመስጠት ፡ ነው ። ሳገሪቱ ፡ ዕድገት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከግል ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ጋር ፡ መዋዋልን ፡ የሚጠይቁ ፡ ብዙ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ያስፈልጋሉ ።

እርግጥ ፡ በጥንት ፡ ዘመን ፡ ለእንግሊዝ ፡ "ኮርፖሬሽን" ፡ እና ፡ ለፈረንሳይ ፡ "ኮምፓኝ" ፡ ይሠራ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ የግል ፡ ቻርተር ፡ ለማውጣት ፡ ይቻል ፡ ነበር ። እያንዳንዱ ፡ ሚኒስቴር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራዎችን ፡ የመቋረጥ ፡ ውሎችን ፡ የሚስማማበትን ፡ የውል ፡ አጻጻፍ ፡ ዓይነት ፡ (ፎርም) ፡ ሊያወጣ ፡ ይችል ፡ ነበር ። ይህ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ መንግሥት ፡ ባገሪቱ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ የሥራ ፡ ድርሻ ፡ በቊጥጥር ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ተቀባይነት ፡ ኖሮትም ፡ ቢሆን ፡ ባሁኑ ፡ ወቅት ፡ ጊዜው ፡ ያለፈበት ፡ ይመስላል ። ያሁኑ ፡ ዘመን ፡ አገሮች ፡ በፊት ፡ ጊዜ ፡ ለየቻርተሮችና ፡ ለውሎች ፡ ተትተው ፡ የነበሩትን ፡ ነገሮች ፡ አሁን ፡ በሕግ ፡ እንዲተዳደሩ ፡ በማድረግ ፡ በበለጠና ፡ የተሻለ ፡ ዝግጅት ፡ ባለው ፡ ዘዴ ፡ እያከናወኑ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ ወደ ፡ መተው ፡ አዘንብለዋል ። ጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ በመሆኑ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተማሩ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ በማነሳቸውና ፡ ባንዳንድ ፡ በየመንግሥቱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሠለጠኑ ፡ ሠራተኞች ፡ ባለመኖራቸው ፡ ላስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ የሚውሉ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦች ፡ ማዘጋጀት ፡ አስፈለገ ። አንድ ፡ አቋም ፡ መዘጋጀት ፡ ነበረበት ፡ ይህም ፡ ሲሆን ፡ በዚሁ ፡ አቋም ፡ ውስጥ ፡ ላስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ ውል ፡ ለሚገቡ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ መጠቀም ፡ እንዲችሉ ፡ በማሰብ ፡ ቦታ ፡ እንዲተውለት ፡ ተደርጓል ።

ስለዚህ ፡ ላስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ የሚውሉ ፡ ደንቦች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር ፡ ተወሰነ ። ይህ ፡ ውሳኔ ፡ የተነሳሳው ፡ የሀገሪቱን ፡ ዕድገት ፡ የሚረዳ ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጋር ፡ በሚደረጉ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ግንኙነት ፡ አስፈላጊው ፡ መተማመን ፡ ይፈጠራል ፡ ተብሎ ፡ በማሰብ ፡ ነው ። ስላስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ደንቦች ፡ የተደረገ ፡ ማብራሪያ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የንግድ ፡ ሥራዎችና ፡ ካፒታል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲገቡ ፡ ይረዳል ፡ ተብሎ ፡ በተለይ ፡ ተስፋ ፡ ተደርጐበታል ።

ውሳኔው ፡ ከተሰጠ ፡ ዘንድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውለው ፡ እንዴት ፡ ነበር ? ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚናገረው ፡ አንቀጽና ፡ በሌሎችም ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ፡ በሚናገሩት ፡ አንቀጾች ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ ደንቦች ፡ ማስገባት ፡ በቂ ፡ አለመሆኑ ፡ ወዲያውኑ ፡ ግልጽ ፡ ሆነ ። ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ አዲስ ፡ መሆናቸውን ፡ ለነርሱም ፡ ግልጽና ፡ የተስተካከሉ ፡ ደንቦች ፡ ማዘጋጀት ፡ ጠቃሚ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ እንደሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ ባንድ ፡ በተለየ ፡ አንቀጽ ፡ ሥር ፡ እንዲሆኑ ፡ ማስፈለጉ ፡ ግልጽ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ደንቦች ፡ ለማውጣት ፡ የሚረዳ ፡ ሞዴል ፡ ከየት ፡ ይገኝ ? ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳችም ፡ ሕግ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ወጥቶ ፡ አያውቅም ። በፈረንሳይ ፡ ሀገር ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የሆኑት ፡ ከኮንሴል ፡ ደኤታ ፡ ውሳኔ ፡ የተገኙ ፡ "ሕጐች" ፡ በሕግነት ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ የተሰበሰቡ ፡ የሉም ። በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ሌሎች ፡ አንዳንድ ፡ አንቀጾችና ፡ ምዕራፎች ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ ሁሉ ፡ ለዚህም ፡ አንቀጽ ፡ መሠረቱ ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ጽሑፎች ፡ ነበር ። ስላስተዳ

ደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ የሚናገር ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ ጽሑፍ ፡ በቅርቡ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ታትሞ ፡ ነበር ።

እኛ ፡ ማድረግ ፡ የነበረብን ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተሰነዘሩትን ፡ አሳቦች ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ ካዘጋጀን ፡ በኋላ ፡ ኮንሴል ፡ ደኤታ ፡ እና ፡ የፈረንሳይ ፡ ደራሲያን ፡ ሳገኟቸው ፡ መፍትሔዎች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ በማሰብ ፡ ማሻሻያዎች ፡ ያስፈልጋቸው ፡ እንደሆን ፡ መጠየቅ ፡ ነበር ።

ኢትዮጵያ ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ከምዕራብ ፡ አውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ትለያለች ። አንድም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ደንብ ፡ (ሕግ) ፡ ቢሆን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተስማሚና ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ሳንጠይቅ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ያገባነው ፡ የለም ። ልክ ፡ ሌሎች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ስናረቅ ፡ እንዳደረግነው ፡ ሁሉ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎችን ፡ አንቀጽ ፡ ስናረቅም ፡ ይህንን ፡ ጥያቄ ፡ ጠይቀናል ። ይህም ፡ ለመሆኑ ፡ በመጨረሻ ፡ ጸድቀው ፡ የወጡት ፡ ደንቦች ፡ በግልጽ ፡ ያሳያሉ ፤ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ አመራር ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ከፈረንሳይ ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ይለያል ። አቋሙ ፡ የሚጠቀምባቸው ፡ ጽንሰ ፡ አሳቦች ፡ የደንቦቹን ፡ አቀራረጽ ፡ የአተረጓጐሙ ፡ መንገድና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚውል ፡ አስቀድሞ ፡ በማመልከቱ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የፈረንሳይ ፡ የሕግ ፡ ጥናት ፡ ምርምር ፡ (የሕግ ፡ ሳይንስ) ፡ ፍሬ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ስለያዛቸው ፡ ደንቦች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከግሪክ ፡ ከስዊስ ፡ ከግብጽ ፡ ወይም ፡ ከእንግሊዝ ፡ የበለጠ ፡ የፈረንሳይን ፡ አይመስልም ። ተስማሚ ፡ እንዲያውም ፡ ተፈላጊ ፡ በሆነው ፡ ልክ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ደንቦች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ፍላጐትና ፡ ስሜት ፡ ጋር ፡ በሙሉ ፡ የተስማሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ መተማመኛዎች ፡ ነበሩ ። ሕጉን ፡ በማሰናዳቱ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ብቻዬን ፡ አልነበርኩም ። እኔ ፡ ያዘጋጀሁት ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቁን ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ረቂቅ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ከተተረጐመ ፡ በኋላ ፡ በመጀመሪያ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚሲዮን ፡ አባሎች ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ከዚያም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ ለመቀበል ፡ የመጨረሻው ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ (ፓርላማ) ፡ ጸንቷል ።

ለብዙዎቹ ፡ አንቀጾች ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ያሠራር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማለፊያ ፡ ነበር ። የኮሚሲዮኑም ፡ ሥራ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ሊቃለል ፡ የቻለው ፡ ከመጀመሪያው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ጋር ፡ በላክሁት ፡ የሕጎችን ፡ መንፈስ ፡ መግለጫ ፡ (ኤክስፖዜ ፡ ደ ፡ ሞቲፍ) ፡ እርዳታ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መግለጫ ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ አንቀጽ ፡ አለመደረጉን ፡ ማስታወስ ፡ ተገቢ ፡ ነው ። "የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች" ፡ የሚለው ፡ አንቀጽ ፡ ለፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ለማቅረብ ፡ በመጨረሻ ፡ ካረቀቅኋቸው ፡ አንቀጾች ፡ አንዱ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለሕጉ ፡ መንፈስ ፡ መግለጫ ፡ አልወጣለትም ። አንቀጹ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ በቀጥታ ፡ ተተረጐመ ፤ በተረፈ ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ የነበረበት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በነገሩ ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ሊመክርበት ፡ ጊዜ ፡ ያል ነበረው ፡ ይመስላል ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ለሕግ ፡ አርቃቂው ፡ ስለዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ምንም ፡ ትችት ፡ ወይም ፡ ጥያቄ ፡ አልተላከም ፤ ከአርቃቂውም ፡ ጋር ፡ አንዳች ፡ ውይይት ፡ አልተደረገም ። የመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ያለምንም ፡ ለውጥ ፡ የኮሚሲዮኑ ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቦ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ያለ ፡ አን

ዳች ፡ ማሻሻያ ፡ ተቀብሎ ፡ ሕግ ፡ አደረገው ። ይህም ፡ አድራጎት ፡ ሊያስገርም ፡ ወይም ፡ ሊያስጋ ፡ አይገባም ፤ ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ ክፍል ፡ (አንቀጽ) ፡ በጣም ፡ የጠለቀ ፡ የሕግ ፡ ምርምር ፡ የሚያስፈልገው ፡ (ቴክኒካል) ፡ ስለ ፡ ሆነና ፡ ስለዚሁም ፡ ክፍል ፡ አንድም ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በተለይ ፡ ትክክል ፡ ፍትሕ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚያምኑበት ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ነው ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ በግልጽ ፡ የሚያስቆጭ ፡ ሁኔታ ፡ ነበር ። ስለሌሎቹ ፡ አንቀጾች ፡ ከኮሚሲዮኑ ፡ ጋር ፡ የተደረገው ፡ ውይይት ፡ ያስገኘው ፡ ጥቅም ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ ካቀረበው ፡ ትችት ፡ በላይ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ረቂቅ ፡ በማሻሻል ፡ ረገድ ፡ ነበር ። ስላረቀቅኳቸው ፡ አንቀጾች ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በተወያየሁበት ፡ ጊዜ ፡ ሥራዬ ፡ ፍጹም ፡ አለመሆኑ ፡ እየተገለጸ ፡ ሄደ ። ስለ ፡ አንቀጽ ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ውይይት ፡ አልተደረገም ፤ የአንቀጹን ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቅ ፡ ከጨረስኩ ፡ ከስድስት ፡ ወራት ፡ ወይም ፡ ከአመት ፡ በኋላ ፡ ለማረም ፡ ሳይመቸኝ ፡ ቀረ ፡ ስለዚህ ፡ ትክክለኛው ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ ሳይሆን ፡ የመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ እንዳለ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ታወጀ ። ከዚህም ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መጓደል ፡ የተነሳ ፡ አንቀጹ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ረገድ ፡ ያልተሟላ ፡ መሆኑ ፡ በፍጹም ፡ አያጠራጥርም ። ይህም ፡ ቢሆን ፡ አንቀጽ ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ መግባቱ ፡ ትልቅ ፡ እድል ፡ ነው ። ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በተመቸ ፡ ጊዜ ፡ ሊሻሻል ፡ ይቻላል ። አሁን ፡ ባለበትም ፡ ሁኔታ ፡ ሕጋዊ ፡ ግንኙነቶች ፡ ዋስትና ፡ እንዲኖራቸው ፡ በማድረግ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የኤኮኖሚ ፡ ዕድገት ፡ ታላቅ ፡ አገልግሎት ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻላል ።

የአንቀጽ ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ቍጥሮች ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ለሚዋዋሏቸው ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ ተፈጻሚ ፡ አይሆኑም ። ተፈጻሚነት ፡ ያላቸው ፡ ከነዚህ ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ፡ ለሚፈልጉት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚያደርጉዋቸው ፡ ውሎች ፡ ተብለው ፡ ለታወቁት ፡ ውሎች ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የሚደረገውን ፡ ልዩነት ፡ በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ ይቀበላል ። ቍጥር ፡ ፫ሺ፻፴፪ ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ውሎችን ፡ ትርጓሜ ፡ ይሰጣል ። የዚሁ ፡ ቍጥር ፡ ንዑስ ፡ ቍጥር ፡ (ለ) ፡ እና ፡ (ሐ) የትኞቹ ፡ ውሎች ፡ ያስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ መሆናቸውን ፡ ለመለየት ፡ የሚያገለግሉ ፡ ጠቅላላ ፡ ማመዛዘኛዎች ፡ (መምሪያዎች) ፡ ይሰጣሉ ፤ ስለነዚህ ፡ ማመዛዘኛዎች ፡ ተፈጻሚነት ፡ የፈረንሳይን ፡ የሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ ለመመልከት ፡ ይቻላል ። ሆኖም ፡ እነዚህ ፡ ማመዛዘኛዎች ፡ አንድ ፡ ውል ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ነው ፡ አይደለም ፡ የሚለውን ፡ ክርክር ፡ ፈጽሞ ፡ ለማስወገድ ፡ አይችሉም ። ስለዚህ ፡ ተዋዋዮች ፡ ወገኖች ፡ ስምምነታቸው ፡ በአንቀጽ ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ፡ ሥር ፡ እንዲውል ፡ ከፈለጉ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ክርክር ፡ ለማስቀረት ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ ቃል ፡ ውላቸውን ፡ "የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል" ፡ ብለው ፡ ሊሰይሙት ፡ መቻላቸውን ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፪ ፡ (ሀ) ፡ ያመለክታል ።

የአንቀጽ ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ መጀመሪያ ፡ ጠቅላላ ፡ ድንጋጌዎች ፡ በሚል ፡ አርዕስት ፡ መሠረታዊ ፡ አሳቦችንና ፡ ትርጓሜዎችን ፡ የያዘ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ተከፍሎ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ ስለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ ሥርዓት ፡ (ቍጥር ፡ ፫ሺ፻፴፩—፫ሺ፻፸፩) ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውሎች ፡ ስለሚያስከትሉት ፡ ውጤት ፡ (ቍጥር ፡ ፫ሺ፻፸፪—፫ሺ፫፻፮) እንዲዘረዝር ፡ ተመድቧል ።

የአተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ ውል ፡ ሲገባም ፡ ሆነ ፣ በሚ ዋዋላቸው ፡ ውሎችም ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ የጸና ፡ እንዲሆን ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ውሉን ፡ ማጽደቅ ፡ ያለበት ፡ እንደሆን ፡ ዝም ፡ ማለቱ ፡ ብቻ ፡ ያለውሉን ፡ አሳብ ፡ እን ደተቀበለ ፡ አያስቆጥረውም ፡ የሚለው ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ በንዑስ ፡ ክፍል ፡ ፭ ፡ ፈቃድን ፡ ስለ ፡ መስጠት ፡ በሚናገረው ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፩ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። በቍ ፡ ሺ፮፻፸፮ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ የተሰጠውን ፡ ደንብ ፡ ላስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ውሎች ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዲሆን ፡ በቍ ፡ ፫ሺ፻፴፪ ፡ እንደገና ፡ ተጽፏል ። ይህ ፡ የተደረገበት ፡ ምክንያት ፡ በቍ ፡ ሺ፮፻፸፮ ፡ የተጠበቁት ፡ የቍ ፡ ሺ፮፻፸፫— ሺ፮፻፸፯ ፡ ሁኔታዎች ፡ ላስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዳ ይሆኑ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ።

ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚናገረው ፡ አንቀጽ ፡ ሥር ፡ የሚገኘው ፡ ቍ ፡ ሺ፮፻፸፮ ፣ አንደኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ የሚጠቀምባቸውን ፡ ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሁኔታዎች ፡ (ግዴታዎች) ፡ ይገልጻል ። እነዚህ ፡ ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሁኔታዎች ፡ በተለይ ፡ በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ውሎች ፡ ውስጥ ፡ የተለየ ፡ ተፈላጊነት ፡ አላቸው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ዘዴ ፡ በመጠቀም ፡ ነው ፡ እንግሊዝ ፡ ከመንግሥት ፡ ጋር ፡ የሚደረጉ ፡ ውሎች ፡ ከሌሎች ፡ ውሎች ፡ የተለዩ ፡ ደንቦች ፡ የሌላቸው ፡ ለማስመሰል ፡ የቻለችው ። ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፭— ፫ሺ፻፴፮ ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ ሊውሉ ፡ የሚችሉትን ፡ ጠቅ ላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ (ግዴታዎች) ፡ ትርጓሜ ፡ ይሰጠዋል ። እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለሚዋዋሏቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ውሎች ፡ በሚስማማው ፡ ዓይነት ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ እንዲዘረዝሯቸው ፡ ስውር ፡ ባል ሆነ ፡ መንገድ ፡ ያሳስባሉ ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ዝርዝር ፡ ደንቦችን ፡ ለመጨመር ፡ አልቻለም ፤ ምክንያቱም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ደንቦች ፡ በጣም ፡ ለተለያዩ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ፍላጐት ፡ ተስማሚ ፡ መሆን ፡ ስላለባቸው ፡ ነው ።

ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፯—፫ሺ፻፴፱ ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ (ግዴታዎች) ፡ ስለሚያስ ከትሉት ፡ ውጤት ፡ ያስረዳሉ ። ሁኔታዎቹ ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈራረም ፡ (አመሠራ ረት) ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፯) ፡ በሚመለከቱበት ፡ ጊዜ ፡ ያላቸው ፡ ውጤት ፣ ስለ ፡ ውሉ ፡ አተረጓጐም ፣ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ ቃልና ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፰ ፡ በሚያመለክቱበት ፡ ጊዜ ፡ ካላቸው ፡ ውጤት ፡ የተለያየ ፡ ይሆናል ። ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈራረም ፡ የሚደረድሩት ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ የመንግሥት ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ያህል ፡ ተፈጻሚነት ፡ (አስገዳጅነት) ፡ ሲኖራቸው ፣ ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፰ ፡ የሚመለከቱት ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ ግን ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ በውሉ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አለባቸው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ እንደገና ፡ በምናነ ብበት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የተደረገው ፡ ልዩነት ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ አይታይም ። በተ ጨማሪም ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፰ን ፡ እና ፡ ቍ ፡ ሺ፮፻፸፮ን ፡ ለማስማማት ፡ በጣም ፡ አዳጋች ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በቍ ፡ ሺ፮፻፸፮ ፡ መሠረት ፣ ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎቹ ፡ የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የደነገጓቸው ፡ ከሆነ ፣ ተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ አስቀድሞ ፡ ያላወቃቸው ፡ ቢሆንም ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናሉ ። ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፰ ፡ በእኔ ፡ በኩል ፡ የሆነ ፡ የብዕር ፡ ስህተት ፡ (ላፕስስ ፡ ካላሚ) ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ምናልባት ፡ መግለጫ ፣ የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ሊቅና ፡ ኮሚሲዮኑ ፡ ውይይት ፡ ቢያደርጉ ፡ ኖሮ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ጠቃሚ ፡ ሊሆን ፡ ይችል ፡ እንደ ፡ ነበርና ፡ ውይይቱም ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ተሳተ ፡ ያሳያል ። ቍ ፡ ፫ሺ፻፴፱ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ባለሥልጣን ፣

ውሉ ፣ ከተፈረመ ፡ በኋላ ፡ በጠቅላላው ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚያደርገው ፡ ለውጥ ፡ የተዋዋዩን ፡ ወገን ፡ መብትና ፡ ግዴታዎች ፡ አይነካም ፡ ይላል ፤ ይህ ፡ ምንም ፡ ማብራሪያ ፡ አያስፈልገውም ፡፡

የሚቀጥሉት ፡ ጥቂት ፡ ቍጥሮች ፡ ደግሞ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ለመግባት ፡ ስላለው ፡ ነጻነትና ፡ አንድ ፡ ውል ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንዲያጸድቀው ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለውሉ ፡ የመጨረሻ ፡ አመሠራረት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማብራሪያዎች ፡ ይሰጣሉ ፡፡ ከነ ዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ አንዱን ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ ለተዋዋ ለው ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ገንዘቦች ፡ ያልተሰጡት ፡ ቢሆንም ፡ ውል ፡ የጸና ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፱) ፡ ልብ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ፡፡ ይህንንም ፡ ቍጥር ፡ ለመጻፍ ፡ የተፈለገው ፡ የዚህን ፡ ተቃራኒ ፡ ውጤት ፡ የሚ ያመጡ ፡ የሚመስሉትን ፡ የእንግሊዝ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፡ በተለይ ፡ እዚህ ፡ ተቀባይነት ፡ እንዳይኖራቸው ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ እንዲሁም ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፰ ፡ ልብ ፡ ብለው ፡ የሚመለከቱት ፡ ቍጥር ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ቍጥር ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንዲያጸድቀው ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ ፡ ውል ፡ ከአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተዋዋለ ፡ ሰው ፡ ያደረገው ፡ ውል ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ የማጽደቁ ፡ ነገር ፡ ያልተ ፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ከውሉ ፡ ግዴታዎች ፡ ውጭ ፡ ለመሆን ፡ ይችላል ፡ ይላል ፡፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ለሚያደርጉት ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ የማዋል ፡ ማሳደር ፡ ተግባር ፡ (ቢሮክ ራሲ) ፡ መከላከያ ፡ ማድረግ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡፡ በመጨረሻም ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፯ ፡ የአስ ተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉን ፡ ሳይፈራረም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ውሉ ፡ ከመ ፈረሙ ፡ በፊት ፡ በተደረገው ፡ ንግግር ፡ ባሳየው ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ ተዋዋዩ ፡ ውሉ ፡ ይፈጸማል ፡ በማለት ፡ ላደረጋቸው ፡ ወጪዎች ፡ ኪሣራ ፡ እንዲጠይቅ ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል ፡፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ኪሣራ ፡ የሚሰጠው ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጥፋት ፡ (ኲልፓ ፡ ኢን ፡ ኮንትሬሔንዶ) ፡ ወይም ፡ ያላግባብ ፡ መ በልጸግ ፡ ሲኖር ፡ ነው ፡፡

ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፱—፫ሺ፪፻፩ ፡ ውሎች ፡ በጨረታ ፡ ስለሚሰጡበት ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ ይናገራሉ ፡፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ይህን ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ አስፈላጊ ፡ ባያደርገውም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ ታዞ ፡ ቢሆ ንም ፡ ባይሆን ፡ በጨረታ ፡ ውል ፡ ለመስጠት ፡ ከወሰነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት ፡፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ የተገኙትን ፡ ደን ቦች ፡ እንዳሉ ፡ ተቀብሎ ፡ አጽድቋቸዋል ፡፡

ስለ ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የተደነገጉት ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፷ ፡ እና ፡ ፫ሺ፻፷፮ ፡ የታቀ ዱት ፡ የሕዝቡን ፡ ጥቅም ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከሚያደርጉት ፡ ስሀተ ትና ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ የማይታመኑ ፡ ሰዎች ፡ ለግል ፡ ጥቅም ፡ ከሚወጥኑት ፡ ስምምነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ ነው ፡፡ እነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ሆነው ፡ አይታዩ ፡ ይሆናል ፡፡ ሆኖም ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ የሊብራል ፡ ኤኮኖሚ ፡ ሁኔታ ዎች ፡ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ ለማስፋፋት ፡ የሚቻል ፡ አይመስልም ፡፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ እንዲታያቸው ፡ እነዚህን ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦች ፡ እያስፋፉ ፡ ሊተረጒሟቸው ፡ ይችላሉ ፡፡

ውል ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የሚናገሩት ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፷፩—፫ሺ፻፷፫ ፡ በውስጣቸው ፡ ሊመለከቷቸው ፡ የሚገባ ፡ ሁለት ፡ ደንቦች ፡ ይዘዋል ፡፡ አንደኛው ፡

(ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፯) ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ አለመፈጸሙ ፡ ተዋዋዩ ፡ ያለበትን ፡ ግዴታዎች ፡ አልፈጽምም ፡ ለማለት ፡ ምክንያት ፡ ሊሆነው ፡ አይችልም ፡ ይላል ። ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፰) ፡ ተዋዋዩ ፡ ዕዳ ፡ ይቻቻልልኝ ፡ ብሎ ፡ የአስተዳደሩን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚችለው ፡ ይቻቻልልኝ ፡ የሚለው ፡ ዕዳ ፡ የቀረጥ ፡ ዕዳን ፡ የሚመለከት ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ነው ። ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፱ንም ፡ መመልከት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፡ ሥልጣኑ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ አስቀድሞ ፡ የተወሰነ ፡ ከሆነ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በራሳቸው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ተዋዋዩን ፡ ግዴታዎቹን ፡ እነርሱ ፡ በወሰኑት ፡ ጊዜ ፡ እንዲፈጽም ፡ ሊያስገድዱት ፡ ይችላሉ ። የቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፱ ፡ ዓላማ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ውል ፡ በሚዋዋሉበት ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ውለታ ፡ አስቀድሞ ፡ ቢደረግ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ ለማስገንዘብ ፡ ነው ።

ስለ ፡ ውል ፡ መሻሻል ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ በሚናገረው ፡ አንቀጽ ፡ በቍ ፡ ፫ሺ፩፻፸፫—፫ሺ፩፻፹ ፡ ውስጥ ፡ ተደንግጓል ። የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከነዚህ ፡ ከጠቅላላዎቹ ፡ ደንቦች ፡ በጣም ፡ ስለሚለዩ ፡ በቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፱—፫ሺ፪፻፹፫ ፡ ውስጥ ፡ ተደርገዋል ። እነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ለአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በተለይ ፡ የተፈቀዱላቸውን ፡ መጠቀሚያዎች ፡ ይደነግጋሉ ፡ ኢምፕሬቪዚኦ ፡ የተባለውን ፡ የሕግ ፡ አሳብ ፡ (ቲኦሪ) ፡ ይቀበላሉ ፤ እንዲሁም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎችን ፡ የሚነኩ ፡ የመንግሥት ፡ አድራጐቶች ፡ ስለሚያስከትሏቸው ፡ ውጤቶች ፡ ደንቦች ፡ አስፍረዋል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹ ፡ እና ፡ ፫ሺ፪፻፹፩ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሚሼል ፡ የሚደግፉትን ፡ “የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኝ ፡ መሆን ፡ አለበት” የሚለውን ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ ይዘዋል ። ውሉ ፡ ለሕዝባዊ ፡ አገልግሎት ፡ የሚጠቅም ፡ ሳይሆን ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ ለፍላጐቱ ፡ የማይስማማ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ ተዋዋዩ ፡ ጥፋት ፡ ባይኖርበትም ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሉን ፡ ሊያፈርስ ፡ ይቻለዋል ። ይህንንም ፡ ሲፈጽሙ ፡ በሕግ ፡ በተሰጣቸው ፡ መብት ፡ መጠቀማቸው ፡ በመሆኑ ፡ እንደ ፡ “ውለታ ፡ ማፍረስ” ፡ ባይቆጠርም ፡ ለተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለባቸው ። ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፩ ፡ እንደገና ፡ ልብ ፡ ተደርጐ ፡ ቢነበብ ፡ ለተዋዋዩ ፡ ኪሣራ ፡ የሚሰጥበት ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ ሰጋስ ፡ ይመስላል ። እዚህ ፡ ላይም ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኮሚስዮን ፡ ውይይት ፡ ቢደረግ ፡ ኖሮ ፡ የመጀመሪያው ፡ ረቂቅ ፡ ሊሻሻል ፡ ይችል ፡ የነበረ ፡ ይመስላል ።

የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መብት ፡ ውሉን ፡ በማስቀረት ፡ ብቻ ፡ አልተወሰኑም ። በራሳቸው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ በውሉ ፡ ውለታ ፡ ላይ ፡ መሻሻያዎችን ፡ ሊያደርጉ ፡ ይችላሉ ፡ (፫ሺ፪፻፷፱) ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ውሉ ፡ እንዲቀርለት ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ። (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፪) ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፹፫—፫ሺ፪፻፹፱ ፡ የኢምፕሬቪዚን ፡ የሕግ ፡ ሐሳብ ፡ (ቲኦሪ) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚ ፡ ያደርጋሉ ። ሕጉ ፡ በእንዴት ፡ ያሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንደሚውልና ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚከፍሉት ፡ ኪሣራ ፡ እንዴት ፡ እንደሚወሰን ፡ ይደነግጋል ። ሕጉ ፡ የሚፈቅደው ፡ ርትዕ ፡ የሆነው ፡ የኪሣራ ፡ አሰተሳሰብ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በራሳቸው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ውልን ፡ በማስቀረት ፡ ወይም ፡ በማሻሻል ፡ ከሚከፍሉት ፡ ኪሣራ ፡ የአስተሳሰብ ፡ መንገድ ፡ በፍጹም ፡ የተለየ ፡ ነው ።

በመጨረሻም ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፪—፫ሺ፻፺፰ ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዓት ፡ (ፌ ፡ ዱ ፡ ፕሪንስ) ፡ ይናገራሉ ። እነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ አዲስ ፡ የሚወጡ ፡ ሕጐችና ፡ ደንቦች ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በተዋዋሏቸው ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ የሚያደርሱትን ፡ የውል ፡ ሚዛን ፡ መናወጥ ፡ ውጤት ፡ እነዚህ ፡ አዲስ ፡ ሕጐችና ፡ ደንቦች ፡ ይቆጣጠራሉ ። የሚደነገጉት ፡ በቀጥታ ፡ ውልን ፡ ለማስቀረት ፡ ወይም ፡ ለማሻሻል ፡ ስላልሆነ ፡ በቍ ፡ ፫ሺ፻፹፱—፫ሺ፻፺፮ ፡ ካሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ይለያሉ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሁኔታዎቹ ፡ ከመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የመነጩ ፡ መሆናቸውንና ፡ ተዋዋዩ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤትም ፡ የዚሁ ፡ መንግሥት ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ መሆኑን ፡ ለመርሳት ፡ የማይቻል ፡ ይመስላል ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ መረዳዳት ፡ ሁኔታ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ የተዋዋለውን ፡ ሰው ፡ መጠበቅ ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ተዋዋዩን ፡ ወገን ፡ በመጠበቅ ፡ ረገድ ፡ አለመቆጠብ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በተፈራረሟቸው ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ያልተረጋጋ ፡ ሁኔታ ፡ ይፈጥር ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሁለቱንም ፡ ሁኔታዎች ፡ ለማስማማት ፡ ጠቅላላ ፡ እና ፡ በተለይ ፡ የሆኑ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ (ውሳኔዎች) ፡ ብሎ ፡ ልዩነት ፡ አበጅቷል ። ጠቅላላ ፡ ጥንቃቄዎችን ፡ ደግሞ ፡ የውሉን ፡ ቃሎች ፡ የሚነኩ ፡ እና ፡ የውሉን ፡ አፈጻጸም ፡ በጣም ፡ ውድ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሁኔታዎች ፡ በማለት ፡ በሁለት ፡ ለይቷቸዋል ። በተለይ ፡ ስለሆኑ ፡ ጥንቃቄዎች ፡ ግን ፡ ልዩነት ፡ የተደረገው ፡ ውሳኔዎችን ፡ ባመነጨው ፡ ባለሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ባለሥልጣን ፡ ተዋዋዩ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ እራሱ ፡ (በቍ ፡ ፫ሺ፻፹፱ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ በቀጥታ ፡ ውሉን ፡ በማሻሻል ፡ ዘዴ ፡ ሳይሆን) ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የአስተዳደር ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ቍ ፡ ሺ፪፻፸፭—ሺ፪፻፸፮ ፡ ስለ ፡ ውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ የደነገጉትን ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፶፩—፫ሺ፻፷፪ ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ አብራርተውና ፡ አሻሽለው ፡ ያቀርባሉ ። ውልን ፡ በግድ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አይገደዱም ፡ (፫ሺ፻፶፩) ፤ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ በአንግሎ ፡ አሜሪካን ፡ ሕግም ፡ (ኮመን ፡ ሎው) ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ የገባበትን ፡ የውል ፡ ግዴታ ፡ እንዲፈጽም ፡ በማዘዣ ፡ (በማንዳመስ) ፡ ለማስገደድ ፡ አይቻልም ። የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከእንግሊዝና ፡ ፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። ቍ ፡ ፫ሺ፻፶፯ ፡ እና ፡ ፫ሺ፻፶፰ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑበት ፡ ምክንያት ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፵፭ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጨመር ፡ ከገፋፋው ፡ ምክንያት ፡ አይለይም ። እንደሌላው ፡ አገር ፡ በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ መጐተት ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩም ፡ ሕግ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ያወገዘውን ፡ ሁኔታ ፡ ሳይመለከተው ፡ ባለማለፉ ፡ በእርግጥ ፡ ከሚደርሱ ፡ ችግሮች ፡ ጋር ፡ የሚታገል ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል ። ስለዚህም ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽሙ ፡ በማዋል ፡ በማሳደር ፡ ነገሩን ፡ የጐተቱ ፡ እንደሆን ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ እንዳችም ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሳያስፈልግ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ በቀጥታ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲታሰብ ፡ ሕጉ ፡ ያዛል ። በተጨማሪም ፡ ከዚህ ፡ ግዴታ ፡ ለመዳን ፡ ሲሉ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የሚስያገቡት ፡ ቃል ፡ የሚሰጠው ፡ ውጤት ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

ከአስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋር ፡ የተዋዋለው ፡ ሰው ፡ የውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲጐተት ፡ ስለሚያደርግበት ፡ ሁኔታ ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፻፶፰ ፡ እና ፡ ፫ሺ፻፶፱ ፡ ይናገራሉ ። እነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ መብቴ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ የባለሥል

ጣኑ ፡ ግዴታ ፡ ነው ፡ ከሚላቸው ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮችና ፡ ከሚፈጥራቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመውጫ ፡ ዘዴዎች ፡ የሕዝቡን ፡ ጥቅም ፡ ለመጠበቅ ፡ የታቀዱ ፡ ናቸው ። የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተዋዋዩ ፡ የውሉን ፡ አፈጻጸም ፡ በመጕተቱ ፡ አንድ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ሳያደርጉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቢያሳልፉም ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፫) ፡ ተዋዋዩን ፡ አይጠቅመውም ፤ እንዲሁም ፡ አቅራቢዎቹ ፡ አስቀድሞ ፡ በአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተፈቀዱ ፡ ካልሆኑ ፡ በስተቀር ፡ የነርሱ ፡ መዘግየት ፡ ተዋዋዩ ፡ በውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ መጕተት ፡ ምክንያት ፡ ከሚደርስበት ፡ ኃላፊነት ፡ አያድነውም ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፻፺፱) ። በመጨረሻም ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፪ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተዋዋዩ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ የተሰጠውን ፡ መብት ፡ በመንፈግ ፡ ቅጣት ፡ ሊወስኑበት ፡ እንደማይችሉ ፡ ይናገራል ። ይህም ፡ ደንብ ፡ በአንቀጽ ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ውስጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቦታ ፡ ተደጋግሞ ፡ ተጽፉል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፭—፫ሺ፪፻፮ ፡ ደግሞ ፡ ውሎችን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ መልቀቅና ፡ ከዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ ስለ ፡ ተስማማ ፡ ሁለተኛ ፡ ተቋራጭ ፡ በመናገር ፡ የጠቅላላውን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ምዕራፍ ፡ ይደምድማሉ ።

የአንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ የሚቀጥሉት ፡ ሦስት ፡ ምዕራፎች ፡ ደግሞ ፡ ለሦስት ፡ ዋና ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ ዓይነት ፡ ተመድበዋል ፤ እነዚህም ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፯—፫ሺ፪፻፵፫) ፡ የመንግሥት ፡ ሥራዎችን ፡ የመቋረጥ ፡ ውል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፬—፫ሺ፪፻፺፮) ፡ እና ፡ ስለ ፡ ዕቃዎች ፡ ማቅረብ ፡ ውል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፯—፫ሺ፫፻፮) ፡ ናቸው ። የሕዝብ ፡ አገልግሎትን ፡ እና ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ኮንሴሲዮንን ፡ ትርጉም ፡ በቍ ፡ ፫ሺ፪፻፯ ፡ ከገለጸ ፡ በኋላ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ በአስተዳደር ፡ በአለሥልጣኖችና ፡ በባለኮንሲሲዮኑ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በመመልከት ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ኮንሴሲዮንን ፡ መወሰን ፡ ይጀምራል ። ሕጉ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ የገባበትን ፡ ግዴታ ፡ አፈጻጸም ፡ ለመቆጣጠር ፡ ስላላቸው ፡ መብት ፡ አንዳንድ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦችን ፡ አስፍሯል ። አንድ ፡ አንዶቹ ፡ ደንቦች ፡ በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ የዋጋና ፡ የታሪፍ ፡ ለውጥ ፡ ለማድረግ ፡ ስለሚፈቅደው ፡ የኮንሴሲዮን ፡ ውል ፡ ቃል ፡ አተረጓጐምና ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አዋዋል ፡ ይደነግጋሉ ። ሌሎቹ ፡ ደንቦች ፡ ደግሞ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በራሳቸው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ የኮንሴሲዮኑ ፡ የመጀመሪያው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ለማድረግ ፡ ስለሚችሉት ፡ ለውጥ ፡ ይናገራሉ ። እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ለአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በተለይ ፡ የተፈቀደላቸውን ፡ መጠቀሚያዎች ፡ ሲሰጡ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ እነዚሁ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አግባብ ፡ ያልሆነ ፡ እርምጃ ፡ እንዳይወስዱ ፡ ይወስኗቸዋል ። በተጨማሪም ፡ ስለ ፡ ኮንሴሲዮኑ ፡ የውለታ ፡ ቃሎች ፡ የትኞቹ ፡ ሊለወጡና ፡ የትኞቹ ፡ ሊለወጡ ፡ እንደማይችሉ ፡ ይዘረዝራሉ ፤ የሚደረገውም ፡ ለውጥ ፡ በባለኮንሴሲዮኑ ፡ ላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ወጪ ፡ ያስከተለ ፡ እንደሆነ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲያገኝ ፡ መብት ፡ ይሰጡታል ። እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ኮንሴሲዮን ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ውል ፡ ሊቆጠር ፡ እንደማይቻል ፡ በግልጽ ፡ ያሳያሉ ። ዓላማው ፡ የሕዝብን ፡ ጠቅላላ ፡ ጥቅም ፡ ለማሟላት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የኮንሴሲዮን ፡ ውል ፡ ተዋዋዮች ፡ የግል ፡ ትርፍ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ ከሚፈልጉባቸው ፡ ውሎች ፡ የተለየ ፡ ነው ።

የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ከጠቅላላው ፡ የውል ፡ ሕግ ፡ የሚለይ ፡ ደንቦች ፡ ያስፈልጉታል ። በጠቅላላው ፡ ውሎች ፡ የሚመለከቱት ፡ ተዋዋይ ፡

ወገኖችን ፡ ብቻ ፡ ነው ። እንደ ፡ እንግሊዝ ፡ ሕግ ፡ (የውል ፡ ግልነት) ፡ እና ፡ እንደ ፡ ፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ (ቍ ፡ ሺ፻፷፭ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ) ፡ በኢትዮጵያም ፡ ሕግ ፡ ውሎች ፡ የሚመለከቱት ፡ በጠቅላላው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖችን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ (ቍ ፡ ሺ፱፻፶፪) ። ሆኖም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ኮንሴሲዮን ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ የሚዋዋሉት ፡ ቢሆንም ፡ ዓላማው ፡ ባገልግሎቱ ፡ የሚጠቀሙትን ፡ የሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ ፍላጐት ፡ ለማርካት ፡ ነው ። የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የውል ፡ ቃሉን ፡ ሲደረድሩ ፡ ለራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ ነው ፡ ቢባልም ፡ በትክክል ፡ አነጋገር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ድርድሩ ፡ እነርሱን ፡ አይመለከትም ። የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ኮንሴሲዮንን ፡ ከሚያስተዳድረው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ደንቦች ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፩—፫ሺ፪፻፳፮) ፡ እነዚህ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ያላቸውን ፡ አቋም ፡ ያስረዳሉ ። በተለይም ፡ ተጠቃሚዎች ፡ (ደንበኞች) ፡ በባለኮንሴሲዮኑ ፡ እኩል ፡ መታየት ፡ አለባቸው ፡ የሚለውን ፡ ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡ ይዘዋል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፫—፫ሺ፪፻፳፱) ፤ እንዲሁም ፡ ባንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ጊዜ ፡ ተጠቃሚዎቹ ፡ በአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ቦታ ፡ ሆነው ፡ ባለኮንሴሲዮኑን ፡ ለመክሰስ ፡ መብት ፡ ይሰጧቸዋል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፭—፫ሺ፪፻፳፮) ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፯ ፡ እና ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፰ ፡ ኮንሴሲዮኑ ፡ ስለሚጸናበት ፡ ጊዜ ፡ ልክና ፡ ስለ ፡ መታደሱ ፡ ያስረዳሉ ። ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፯ ፡ የኮንሴሲዮኑ ፡ ጊዜ ፡ ከሰላሳ ፡ ዓመታት ፡ መብለጥ ፡ የለበትም ፡ ብሎ ፡ ያውጃል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የሕገ ፡ መንግሥትን ፡ ያህል ፡ አስገዳጅነት ፡ የለውም ። ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፯ ፡ ይህን ፡ ሲል ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ከሰላሳ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ለመስጠት ፡ በቂ ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ የምክር ፡ ቤቱን ፡ (የፓርላማን) ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

የኮንሴሲዮኑን ፡ ሂሣብ ፡ ማጣራት ፡ የጠጠሩ ፡ ችግሮችን ፡ (ፕሮብሌሞችን) ፡ ስለሚያስነሳ ፡ ይህንኑ ፡ ለመቋቋም ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፳፱—፫ሺ፪፻፷፩ ፡ ተደንግገዋል ። የባለኮንሴሲዮኑን ፡ ተገቢ ፡ ጥቅሞች ፡ መጠበቅ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አይሆንም ። የኮንሴሲዮኑ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ማለቂያው ፡ ሲደርስ ፡ ባለ ፡ ኮንሴሲዮኑ ፡ የሚያደርገው ፡ የግዴለሽነት ፡ ሥራ ፡ መከልከል ፡ አለበት ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ የሕዝቡ ፡ አገልግሎት ፡ በመንግሥትም ፡ ሆነ ፡ በአዲስ ፡ ባለ ፡ ኮንሴሲዮን ፡ እጅ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ መቀጠሉ ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት ። ባለ ፡ ኮንሴሲዮኑ ፡ ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋር ፡ በመሠረተው ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ሰጭውን ፡ በባለ ፡ ኮንሴሲዮኑ ፡ እግር ፡ የሚዳርገው ፡ (የሚከተለውን) ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፬ ፡ ይህ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ የገንዘብን ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ እና ፡ ስለ ፡ መዳረግ ፡ የተጻፉት ፡ ደንቦች ፡ (ቍ ፡ ሺ፱፻፷፪—ሺ፱፻፸፩) ፡ ተፈጻሚ ፡ ከሚሆኑባቸው ፡ ተራ ፡ ውሎች ፡ በመሠረቱ ፡ የተለየ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል ።

ለአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ኮንሴሲዮን ፡ መልሶ ፡ ለመግዛት ፡ የተሰጣቸው ፡ መብት ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፯ ፡ እና ፡ ፫ሺ፪፻፷፱) ፡ በራሳቸው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ በቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺ ፡ መሠረት ፡ ማንኛውንም ፡ የአተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ ለማስቀረት ፡ ከተሰጣቸው ፡ መብት ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ኮንሴሲዮኑን ፡ መልሶ ፡ የመግዛቱ ፡ መብት ፡ ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺፩ ፡ በሚዘረዝራቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ፤ የኪሣራውም ፡ አሰጣጥ ፡ የሚወሰነው ፡ በቍ ፡ ፫ሺ፪፻፺ ፡ መሠረት ፡ አይደለም ።

ስለ ፡ ባለኮንሴሲዮን ፡ መብት ፡ እጦት ፡ (ዴሼአንስ) ፡ እና ፡ ስለ ፡ ማስያዝ ፡ በሁለተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የሚገኙት ፡ ቍጥሮች ፡ ይናገራሉ ። እነ

ዚህ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሊያዛቸው ፡ የሚችሉት ፡ ቅጣቶች ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ ተገቢ ፡ መሆናቸውን ፡ በመጨረሻ ፡ መወሰኑ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፋንታ ፡ ነው ። አስፈላጊ ፡ ከሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እነዚህን ፡ ቅጣቶች ፡ ሰርዞ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ባለኮንሴሲዮኑ ፡ ለደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ሊያዝ ፡ ይችላል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፮) ።

ስለ ፡ <u>የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ የመቋረጥ ፡ ውል</u> ፡ የሚናገረው ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ለየትኞቹ ፡ ውሎች ፡ ተፈጻሚ ፡ እንደሚሆንና ፡ ትርጉምም ፡ በመስጠት ፡ ይጀምራል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፬—፫ሺ፪፻፵፭) ። ለጥቅም ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖቹ ፡ ተቋራጮችን ፡ በውድድር ፡ ለመምረጥ ፡ በፈለጉ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አመሠራረት ፡ ይኸው ፡ ምዕራፍ ፡ ይናገራል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፵፯—፫ሺ፪፻፵፱) ።

የምዕራፉ ፡ ተከታታይ ፡ ቍጥሮች ፡ ደግሞ ፡ ለአስተዳደሩ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራዎችን ፡ ውል ፡ አፈጻጸም ፡ ለመቆጣጠርና ፡ ለመምራት ፡ የሚያስችለውን ፡ መብት ፡ ይሰጣሉ ። እነዚህን ፡ ቍጥሮች ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፶—፫ሺ፪፻፶፰) ፡ ስለማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ከሚናገሩት ፡ ቍጥሮች ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፲፱—፫ሺ፵፡ ጋር ፡ ብናስተያያቸው ፡ የመንግሥት ፡ ሥራዎችን ፡ የመቋረጥ ፡ ውል ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ በመሆኑ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ውል ፡ እንደሆነ ፡ መገንዘብ ፡ እንችላለን ። የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ውል ፡ በሚዋዋሉበት ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ እንደ ፡ ግል ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ አይደሉም ። ከሌላ ፡ ማዕዘን ፡ በኩል ፡ ሆነን ፡ ብንመለከት ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚዋዋሉት ፡ ውል ፡ የሕዝቡን ፡ ጥቅም ፡ የሚነካ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ሊቆጠር ፡ አይገባም ። እርግጥ ፡ ነው ፡ አግባብ ፡ ያልሆነ ፡ እርምጃ ፡ ለመውሰድ ፡ የሚያስችለው ፡ ሥልጣን ፡ መፈቀድ ፡ የለበትም ፤ ግን ፡ በሁለቱ ፡ ተዋዋይ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የውል ፡ ሚዛን ፡ ስናመጣጥን ፡ ውሉ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውል ፡ መሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ይኖርብናል ። አንድ ፡ የግል ፡ ነዋሪ ፡ እንዲሠራለት ፡ የተዋዋለውን ፡ እንዲመራ ፡ በማይቆይበት ፡ ጊዜ ፡ ሲያቅተው ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ባንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ጊዜ ፡ የሥራው ፡ የበላይ ፡ አዛዥነታቸው ፡ መጠበቅ ፡ አለበት ። ለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊውን ፡ ሰው ፡ ማሰልጠንና ፡ መቆጣጠር ፡ የሚያስችሉ ፡ ደንቦች ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፡ ማውጣት ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እነዚህን ፡ ደንቦች ፡ ለማውጣት ፡ ሞክሯል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፩—፫ሺ፪፻፸፫ ፡ ስለ ፡ ዋጋ ፡ አከፋፈል ፡ ደንቦች ፡ ይዛል ። በመጀመሪያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ያከፋፈል ፡ ዘዴዎች ፡ ተዘርዝረዋል ። የሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ባንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ጊዜ ፡ ሲዘገዩ ፡ ለተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ መተማመኛ ፡ ይሰጣሉ ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፯) ፤ እንዲሁም ፡ ተዋዋዩ ፡ ወገን ፡ በግዴታው ፡ መሠረት ፡ ለፈጸማቸው ፡ ነገሮች ፡ ከሂሣቡ ፡ ላይ ፡ የሚታሰብ ፡ ገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ የመቀበል ፡ መብት ፡ ይሰጡታል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፷፱ ፡ እና ፡ ፫ሺ፪፻፸) ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ላልተሠራ ፡ ሥራ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚከፈልበትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ወስኗቸዋል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፩) ።

ስለ ፡ ሥራዎች ፡ ርክክብ ፡ ጉዳይ ፡ ደግሞ ፡ በቍ ፡ ፫ሺ፪፻፸፬—፫ሺ፪፻፹፩ ፡ ተደንግጓል ። በእነዚህ ፡ ቍጥሮች ፡ ውስጥም ፡ ስለ ፡ አሠራር ፡ ጉድለት ፡ መድኅንነት ፡ ደንቦች ፡ ይገኛሉ ።

በክፍል ፡ ፯ ፡ ውስጥ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ውል ፡ የሚሻሻሉባቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ደንቦች ፡ ሰፍረዋል ። በራሳቸው ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ያስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ውሉን ፡ ሊያሻሽሉ ፡ ይችላሉ ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፸፫—፫ሺ፩፻፸፮) ። ሥራ ፡ ተቋራጭ ፡ ውሉን ፡ በሚፈጽምበት ፡ ጊዜ ፡ ታይቶ ፡ የማይታወቅ ፡ ውሉም ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ያልታሰቡ ፡ እክል ፡ ያጋጠመው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ውሉ ፡ እንዲሻሻል ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፸፯—፫ሺ፩፻፸፱) ። ተቋራጩ ፡ ውሉን ፡ ለማስቀረት ፡ መቻሉና ፡ የሚጠይቀውም ፡ የኪሣራ ፡ መጠን ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሷል ።

ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፸፰—፫ሺ፩፻፹፪ ፡ ደግሞ ፡ ግዴታውን ፡ በሚገባ ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በተቋራጩ ፡ ላይ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሊወስዱ ፡ የሚችሉትን ፡ እርምጃዎች ፡ ይዘረዝራሉ ፤ እነዚህም ፡ እርምጃዎች ፡ በሚገባ ፡ ያልተሠራውን ፡ ሥራ ፡ በሥራ ፡ መሪ ፡ (በመንግሥት ፡ ቁጥጥር) ፡ ሥር ፡ ማድረግና ፡ ውሉን ፡ እንደገና ፡ ማጫረት ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ እርምጃዎች ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚቆጣጠሯቸው ፡ ቢሆንም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰርዟቸው ፡ አይችሉም ። የተወሰዱት ፡ እርምጃዎች ፡ ተገቢ ፡ ያልሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለተቋራጩ ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፍሉ ፡ ከማድረግ ፡ (ቍ ፡ ፫ሺ፩፻፹፪) ፡ በስተቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ አይችሉም ።

የምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ ፯ ፡ ውልን ፡ ለዋስትና ፡ መያዣነት ፡ ስለ ፡ ማስተላለፍ ፡ ይናገራል ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ዘዴ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ሥራው፣ ገንዘብ ፡ ማግኘቱንና ፡ መፋጠኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይም ፡ በመብት ፡ ተቀባዩና ፡ በዋናው ፡ ተቋራጭ ፡ ውስጥ ፡ ተቋራጭ ፡ በሆነው ፡ ሰው ፡ አቋም ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ተደርጓል ።

የዕቃዎች ፡ ማቅረብ ፡ ውል ፡ ያሉት ፡ የተለዩ ፡ ጠባዮች ፡ ከመንግሥት ፡ ሥራዎችን ፡ የመቋረጥ ፡ ውልና ፡ ከሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ኮንሴሲዮን ፡ ውል ፡ ጠባዮች ፡ ያነሱ ፡ ናቸው ። ሆኖም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተለየ ፡ ቦታ ፡ ተሰጥቶታል ። <u>በአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች</u> ፡ አንቀጽ ፡ ሥር ፡ በመጨረሻው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለዚሁ ፡ ውል ፡ አሥር ፡ ቍጥሮች ፡ ተደንግገዋል ።

ባጭሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎችን ፡ የሚመለከታቸው ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ በእርግጥ ፡ ከፍጹምነት ፡ የራቁ ፡ ናቸው ፤ ለዚህም ፡ አንድ ፡ ምክንያት ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ተናግረናል ። በተጨማሪም ፡ ይህ ፡ ክፍል ፡ ገና ፡ ያልተረጋገጠና ፡ ያልተረጋጋ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንዴት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ለመቆጣጠር ፡ ይቻላል ፡ በማለት ፡ ክርክር ፡ ይነሳ ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ክርክር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለሌላው ፡ የሕግ ፡ ክፍል፣ የሕግ ፡ መሰናዶዎች ፡ (ኮዲፊኬሽን) ፡ በሚያደርጉበት ፡ አገሮች ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሕግ ፡ ለምን ፡ በሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ መልክ ፡ እንዳልተሰናዳ ፡ ለመግለጽ ፡ የሚቀርብ ፡ ነው ። የሕግ ፡ መሰናዶ ፡ ለማድረግ ፡ ከፍርድ ፡ የተገኙ ፡ "ሕጎች" ወይም ፡ የአስተዳደር ፡ ልምድ ፡ የተጨበጠ ፡ መሠረት ፡ በማይሆኑበት ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባሉ ፡ አገሮችማ ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ የበለጠ ፡ የጸና ፡ አይሆንምን ?

ይህን ፡ ችግር ፡ በሰፊው ፡ ተነጋግረንበት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ክርክሩን ፡ ትተን ፡ ለማለፍ ፡ ወሰን ። የአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ እንኳን ፡ ከተጀመረ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ በጠቅላላው ፡ የሕግ ፡ አከፋፈል ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ መጭ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ አንዳንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ያላቸውን ፡ የተረጋገጠ ፡ ሁኔታ ፡ ያህል ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግ ፡

እንደሌለው ፡ ምንም ፡ አያጠራጥርም ። በቅርብ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የመንግሥት ፡ የሥራ ፡ ክፍያ ፡ በመለወጡ ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ የተረጋገጠ ፡ በመሰለበት ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ መሠረቱ ፡ ተናጋ ። በዚህ ፡ ወደፊት ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ በማይታወቅበት ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ መጨረሻው ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ለማወቅ ፡ የሚችል ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግን ፡ እንዳናዳብረው ፡ ምክንያት ፡ የሚሆን ፡ ነውን ? ሕግ ፡ አውጪውስ ፡ ቢሆን ፡ አሁን ፡ ላለው ፡ ኅብረተሰብ ፡ ደንቦች ፡ ለማውጣት ፡ የዳኞችን ፡ ያህል ፡ ችሎታ ፡ አለውን ?

የመጨረሻው ፡ ጥያቄ ፡ በአሉታ ፡ የተመለሰ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከልምድ ፡ (ባህል) እና ፡ ከፍርድ ፡ የተገኘ ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ ተጽፎ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ የሕጎችን ፡ መዳበር ፡ ይገታል ፡ በሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ላይ ፡ የተመረኮዘ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ይህ ፡ ሳቪኚ ፡ በጠቅላላው ፡ የሕግ ፡ መሰናዶን ፡ በመሠረቱ ፡ ሳይሆን ፡ በሁኔታው ፡ ሲቃወቅም ፡ የተመረኮዘው ፡ አስተሳሰብ ፡ ያልተረጋገጠ ፡ ነው ፤ እንዲያውም ፡ የዚህ ፡ ተቃራኒው ፡ ልክ ፡ ይመስላል ። ለኢትዮጵያ ፡ ተዘርዝሮ ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ በቂ ፡ ጠቅላላ ፡ ደንቦችን ፡ ስለ ፡ ያዘ ፡ ለአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የመዋዋል ፡ ተግባራቸው ፡ በማይገባ ፡ አኳኋን ፡ እንዳይታገት ፡ ሰፊ ፡ ቦታ ፡ ተትቶላቸዋል ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የአስተዳደር ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ የሚመራ ፡ የጥንት ፡ ልምድ ፡ ስለሌለና ፡ ዳኞችም ፡ አሁን ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ስላይደሉ ፡ ከሌሎች ፡ አገሮች ፡ ይልቅ ፡ እዚህ ፡ ለአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ መምሪያ ፡ የሚሆን ፡ መሠረት ፡ መጣል ፡ በበለጠ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ በኮመን ፡ ሎው ፡ (የእንግሊዝና ፡ የአሜሪካን ፡ ሕግ) ፡ እና ፡ በፈረንሳይ ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ ሁሉ ፡ የአስተዳደርን ፡ ሕግ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በኩል ፡ ለማዳበርና ፡ ለማስፋፋት ፡ ጊዜና ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮችም ፡ የሏትም ።

እቋሟን ፡ በቶሎ ፡ ለማደስና ፡ ዘመናዊ ፡ በማድረግ ፡ የሕዝቧን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ለማሻሻል ፡ ለምትፈልግ ፡ ሀገር ፡ የሕግ ፡ መሰናዶ ፡ ፍጹም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተነገረውን ፡ ያህል ፡ ለአስተዳደር ፡ ሕግም ፡ እውነትነት ፡ አለው ። የሕጉ ፡ አመሠራረት ፡ ዳኞች ፡ በሚሰጡት ፡ ፍርድ ፡ ቢሆን ፡ በጥቃቅን ፡ ትርጉሞች ፡ የበለጸገ ፡ ሆኖ ፡ ለኅብረተ ፡ ሰቡም ፡ ፍላጐት ፡ የሚስማማ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ፡ ሆኖም ፡ ይህ ፡ ጠቃሚነት ፡ የተረጋገጠ ፡ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ የዳኞች ፡ ዝብዘባ ፡ በአንዳንድ ፡ ዘመናት ፡ ብዙ ፡ መስዋዕት ፡ ጠይቋል ። በኮመን ፡ ሎው ፡ ሀገሮች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ጣልቃ ፡ ይገባ ፡ ኖሮ ፡ ሕጋቸው ፡ በጠነጠኑ ፡ ጽንሰ ፡ ሐሳቦችና ፡ ደንቦች ፡ ተውጠው ፡ ይቀሩ ፡ ነበር ። በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በእውቅ ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ ልብስ ፡ ይስማሚታል ፡ ተብሎ ፡ በዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ሕጉን ፡ ለማዳበር ፡ መጠበቅ ፡ አትችልም ።

ስለዚህ ፡ አንድ ፡ አስቀድሞ ፡ የተዘጋጀ ፡ ሕግ ፡ ሰጥተናል ። ሥራውን ፡ ለመጀመር ፡ ከማመንታታችን ፡ ይበልጥ ፡ ሥራውን ፡ መፈጸማችን ፡ አያሳፍረንም ። ግን ፡ በእርግጥም ፡ የሕጉ ፡ መሻሻያ ፡ መንገድ ፡ ምንም ፡ አልተዘጋም ። በሌላው ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ ዳኞችና ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ሁኔታዎቹ ፡ ሊያስማሙት ፡ ይችላሉ ። ወደፊት ፡ ሕጋቸውን ፡ የሚገነቡበት ፡ መሠረት ፡ አስተሳሰባቸውንና ፡ ክርክራቸውን ፡ የሚመሠርቱበት ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦች ፡ ሥራቸውንም ፡ የሚመሩበት ፡ አቋም ፡ ለማስገኘት ፡ መርዳታችንን ፡ በእርግጥ ፡ እናምናለን ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ሊያደርግ ፡ የሚችለው ፡ ይህንኑ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

* ይህ ፡ አንቀጽ ፡ በሜላንገ ፡ ሰያማ—ላሰ ፡ ውስጥ ፡ እንዲታተም ፡ በፈረንሳይኛ ፡ የተጻፈ ፡ ሲሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ እንዲታተም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ረዳት ፡ ፕሮፌሰርና ፡ ረዳት ፡ ዲን ፡ በሆኑት ፡ በማይክል ፡ ኪንድረድ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ተተረጐመ ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ተርጓሚ ፡ የጨመራቸው ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ዎች ፡ የተመለከቱት ፡ በሆሄያት ፡ ሲሆን ፤ በአረብኛ ፡ ቍጥሮች ፡ የተመለከቱት ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻዎች ፡ አንቀጹ ፡ በፕሮፌሰር ፡ ዳቪድ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የነበሩት ፡ ናቸው ።

## የግርጌ ፡ ማስታወሻ ።

** በፓሪስ ፡ የሕግና ፡ የአገር ፡ ምጣኔ ፡ ሀብት ፡ ጥናት ፡ ፋኩልቲ ፡ የሕግ ፡ ፕሮፌሰር ።

1 የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የታወጀው ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሆን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ የጀመረው ፡ ከመስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሕግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ሕግ ፡ ታትሞ ፡ የሚወጣበት ፡ ኦፊሴላዊ ፡ ጋዜጣ ፡ በሆነው ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በተለይ ፡ በወጣው ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል ። ሆኖም ፡ የሕጉ ፡ ሁለቱም ፡ጽሑፎች ፡ የተተረጐሙት ፡ የሕጉ ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቅ ፡ በተጻፈበት ፡ ከፈረንሳይኛ ፡ ነው ። እኛም ፡ ይኸንን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ለማዘጋጀት ፡ በመመረጣችን ፡ ክብር ፡ ይሰማናል ። በኋላም ፡ ሕጉ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ደ ፡ ላምፕየር ፡ ዲቲዮፒ ፡ (ሊብሬ ፡ ጄኔራል ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ጁሪስፕሩዳንስ ፡ ፲፱፻፷፱) ፡ ተብሎ ፡ ታትሟል ። በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ እትሞች ፡ ውስጥ ፡ ያልተጨመረው ፡ በፊደል ፡ ቅደም ፡ ተከተልነት ፡ የተዘጋጀ ፡ ዝርዝር ፡ ማውጫ ፡ በፈረንሳዩ ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ።

2 የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአምስት ፡ መጻሕፍት ፡ የተከፋፈለ ፡ ነው ። ፩ኛ ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ፪ኛ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ዘመድና ፡ ስለ ፡ ውርስ ፡ (አወራረስ) ፡ ፫ኛ ፡ ስለ ፡ ንብረት ፡ ፬ኛ ፡ ስለ ፡ ግዴታዎች ፡ ፭ኛ ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ውሎች ። ይህ ፡ ሕግ ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በዋለው ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ የተሟላ ፡ ነው ። የንግድ ፡ ሕጉም፡ በፈረንሳይኛ ፡ ኮድ ፡ ደ ፡ ኮሜርስ ፡ ደ ፡ ላምፕየር ፡ (ለ ፡ ሊትሮፒ) ፡ ደ ፡ ዲትዮፒ ፡ ፲፱፻፷ ፡ (ሊብሬር ፡ ጄኔራል ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ ዲቲዮፒ ፡ ኤ ፡ ደ ፡ ጁሪስፕሩዳንስ ፡ ፲፱፻፷፭) ፡ ተብሎ ፡ ታትሟል ። የንግድ ፡ ሕጉ ፡ የመጀመሪያ ፡ ረቂቅ ፡ የተዘጋጀው ፡ በሁለት ፡ የፈረንሳይ ፡ የሕግ ፡ ምሁሮች ፡ ነው ። እነሱም ፡ ፕሮፌሰር ፡ እስካራራና ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዠፍሬ ፡ ናቸው ።

(ሀ) አንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ተቀጣይ ፡ ሆኖ ፡ ወጥቷል ።

(ለ) ዴ ፡ ኮንትራ ፡ ቪሳ ፡ አ ፡ አን ፡ ትራንስፌር ፡ ደ ፡ ድርዋ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ "ኮንትራክትስ ፡ ሪሌቲንግ ፡ ቱ ፡ ዚ ፡ አሳይንመንት ፡ አፍ ፡ ራይትስ" ተብሎ ፡ ተተርጉሟል ።

(ሐ) ዴ ፡ ዴ ፡ ኮንትራት ፡ ቪሳን ፡ አ ፡ ላ ፡ ግራንድ ፡ ኡሳዥ ፡ ኡ ፡ ላ ፡ ዡዊሳንስ ፡ ዲውን ፡ ሾዝ ፡ ይህ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ "ኮንትራክትስ ፡ ፎር ፡ ዘ ፡ ካስቶዲ ፡ ዩዝ ፡ ኤንድ ፡ ፓዜሽን ፡ አፍ ፡ ቻትልስ" ፡ ተብሎ ፡ ተተርጉሟል ።

3 ምንም ፡ እንኳን ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚዋዋላቸው ፡ ውሎች ፡ ሁሉ ፡ በአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ እንደሚተዳደሩ ፡ አድርገን ፡ ብንቆጥራቸውም ፡ የአስተዳደር ፡ ሕግ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚዋዋላቸውን ፡ አንዳንድ ፡ ውሎች ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ሲመለከታቸው ፡ ሌሎቹን ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ አስተያየት ፡ ሊመለከታቸው ፡ የማይችልበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ፡፡ አንዳንዶቹን ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስር ፡ ሲያደርጋቸው ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕግ ፡ እንዳረገው ፡ ለሌሎቹ ፡ የተለየ ፡ ሕግ ፡ ሊፈጥርላቸው ፡ ይችላል ፡፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚቀረው ፡ ችግር ፡ ሁለቱን ፡ የውል ፡ ዓይነቶች ፡ ለመለየት ፡ የሚያስችለውን ፡ ማመዛዘኛ ፡ የመወሰኑ ፡ ነገር ፡ ነው ፡፡

4 ከኮመን ፡ ሎው ፡ ጋር ፡ ለማነጻጸር ፤ ጄይ ፡ ሚሼል ፡ ዘ ፡ ኮንትራክትስ ፡ ኦፍ ፡ ፓብሊክ ፡ ኦቶሪቲስ ፡ (፲፱፻፷፩) ፡ ኤች ፡ ስትሬት ፡ ጋቨርንመንት ፡ ላያቢሊቲ ፡ (ኬምብሪጅ ፡ ፲፱፻፶፫) ፤ ጂ ፡ ላንግሮድ ፡ "የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውሎች ፤ በማነጻጸር ፡ የተደረገ ፡ ጥናት" ፡ አሜሪካን ፡ ጆርናል ፡ ኦፍ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ሎው ፡

5 የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ በመጽሐፍ ፡ መልክ ፡ ከመሰናዳቱ ፡ በፊት ፡ ወደቅጥ ፡ የለሽነት ፡ የተቃረበ ፡ ነበር ፡፡ ኢትዮጵያን ፡ ለክርስቲያኖች ፡ የቤተ ፡ ክህነትን ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ የፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ የበላይነት ፡ ለእስላሞች ፡ የእስላም ፡ ሕጎችን ፡ የበላይነት ፡ ሲያውቁ ፡ በውን ፡ ግን ፡ የኖሩት ፡ በእርግጥ ፡ ምን ፡ መሆናቸው ፡ ባልታወቁት ፡ የበላይነታቸው ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በሚደረጉ ፡ ለውጦች ፡ ምክንያት ፡ ያልተረጋጋና ፡ ከቀበሌ ፡ ወደ ፡ ቀበሌ ፡ በሚለዋወጡት ፡ ባህሎች ፡ ነበር ፡፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባህላዊ ፡ ሕግ ፡ ሲ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፤ ዲሪቶ ፡ ኮንስዌቱዲናሪዩ ፡ ዴሌሪትሪያ ፡ (ሮማ ፡ ፲፱፻፲፰) ፡ እና ፡ ኤፍ ፡ ኡስቲኒ ፡ ዲሪቶ ፡ ኩንሱዌቱዲናሪዩ ፡ ዴሌሪትሪያ ፡ (አሥመራ ፡ ፲፱፻፶፪) ፡ ጋር ፡ አነጻጽረው ፡፡ የማሪያን ፡ (ኤን) ፡ ዘ ፡ ዲሻል ፡ ሲስተም ፡ ኤንድ ፡ ዘ ፡ ሎውስ ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (ሮተርዳም ፡ ፲፱፻፶፭) ፡ የሚለው ፡ መጽሐፍ ፡ የተመለከተው ፡ ስለ ፡ አንዳንድ ፡ ዘመናዊ ፡ ሕጎች ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በተለይም ፡ በመንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ንግድ ፡ ግምሩክና ፡ እነሱን ፡ በመሳሰሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ነው ፡፡

6 የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከታወጀ ፡ ወዲህ ፡ የአስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤትን ፡ ውሎች ፡ የሚመለከቱት ፡ የተሚሉ ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ ሕጎቹን ፡ በሚጠቀልሉ ፡ መጻሕፍት ፡ በቼኮስላቫኪያና ፡ በጀርመን ፡ ዲሞክራቲካዊ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ታትመዋል ፡፡ እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ አልነበሩም ፡፡ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ ሕጎች ፡ የተዘጋጁት ፡ በምጣኔ ፡ ሀብት ፡ አቅዋማቸውና ፡ በፖለቲካ ፡ ፍልስፍናቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በጣም ፡ ለሚለዩት ፡ "ለሶሺያሊስት" ፡ አገሮች ፡ በመሆኑ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተስማሚ ፡ ሞዴሎች ፡ ሊሆኑ ፡ አይችሉም ፡ ነበር ፡፡

(መ) ኮንሴ ፡ ዴታ ፡ የፈረንሳይ ፡ የአስተዳደር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቁንጮ ፡ ነው ፡፡ እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ችሎቶች ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ፡፡

7 በተለይ ፡ የምንጠቅሰው ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኃላፊነት ፡ የሚለውን ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ፡፡ ፺፩፮ ፡ ቍጥሮች ፡ ያሉትን ፡ ይህን ፡ ምዕራፍ ፡ ስናዘጋጅ ፡ የሚከተሉትን ፡ ሁለት ፡ መጻሕፍት ፡ በሰፊው ፡ ተጠቅመንባቸዋል ፡፡ አር ፡ ሮዲየር ፡ ላ ፡ ሪስፖንሳቢሊቲ ፡ ሲቪል ፡ (ፓሪስ ፡ ፲፱፻፶፪) ፡ እና ፡ ኢ ፡ ጄንክስ ፡ ዳይጄስት ፡ ኦፍ ፡ ኢንግሊሽ ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ (፬ኛ ፡ እትም ፡ ለንደን ፡ ፲፱፻፵፯) ፡፡

8 ኤ ፡ ሉባዳር ፡ ትራቴ ፡ ቴዎሪክ ፡ ኤ ፡ ፕራቲክ ፡ ዴ ፡ ኮንትሪት ፡ አድሚኒስትራቲፍ፡ (፫ ቮልዩሞች ፡ ፓሪስ ፡ ፲፱፻፶፮) ።

9 አንቀጽ ፡ ፬ን ፡ (ስለ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ ዝምድና) ፡ አንቀጽ ፡ ፯ን ፡ (ስለ ፡ ግል ፡ ሀብት) ፡ አንቀጽ ፡ ፱ን ፡ (በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ በኅብረት ፡ ስለ ፡ መጠቀም) ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ን ፡ (ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ ኃላፊነትና ፡ ያላግባብ ፡ ስለ ፡ መበልጸግ) ፡ ኮሚስዮኑና ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ብዙ ፡ ማሻሻያዎች ፡ አድርገውባቸዋል ። ኮሚስዮኑና ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ ጥልቅ ፡ ያልሆኑ ፡ ለውጦች ፡ ሳያደርግ ፡ ከቀሩት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ከግማሽ ፡ በላይ ፡ የሆኑትን ፡ በመጠኑ ፡ አሻሽሏቸዋል ።

(ሠ) ስለደንቦቹ፡አመጣጥና፡የደንቦቹን፡አገልግሎት፡የሚገልጽ፡ማብራሪያ ።

10 የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሰንድ ፡ ቍጥር ፡ ፷፬ ፡ ሰኔ ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የተላከ ።

11 ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ እንዲታወጅ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ መዘጋጀት ፡ እንደነበረበት ፡ ማስታወስ ፡ ያስፈልጋል ።

12 ይህ ፡ የሆነው ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ለሆኑ ፡ አንቀጾች ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከአንቀጽ ፡ ፲፬ ፡ በስተቀር ፡ ልጠቅሰው ፡ የምችለው ፡ አንቀጽ ፡ ፫ን ፡ (በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ስለ ፡ ተሰጣቸው ፡ ማኅበሮችና ፡ ለልዩ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተመደቡ ፡ ንብረቶች) ፡ አንቀጽ ፡ ፲ን ፡ (ስለ ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ መዝገብ) ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱ን ፡ (ስለ ፡ እንደራሴነት) ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፳ን ፡ (ስለ ፡ ግልግልና ፡ ስለ ፡ ስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ ውል) ፡ ነው ። ይህም ፡ ቢሆን ፡ ለአንቀጽ ፡ ፫ ፡ ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ኮሚስዮኑ ፡ ኃላፊነት ፡ ቢኖረውም ፡ ያደረጋቸው ፡ ለውጦች ፡ እስከዚህም ፡ ብዙ ፡ አይደለም ።

13 ይህ ፡ አነጋገር ፡ ከመቆጨት ፡ የተነሳ ፡ ነው ። ለኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የላከኋቸውን ፡ የመጨረሻ ፡ አንቀጾች ፡ (አንቀጽ ፡ ፳፩ ፡ ስለ ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሰንድ ፡ ቍጥር ፡ ፹፯ ፡ የካቲት ፡ ፲፭ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) እና ፡ አንቀጽ ፡ ፳፪ ፡ ስለዚህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የሚጸናበት ፡ ጊዜና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለመዋሉ ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሰንድ ፡ ቍጥር ፡ ፺፪ ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፭ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ለመተርጐምና ፡ ለመመርመር ፡ ጊዜ ፡ አልነበረም ። አንቀጽ ፡ ፳፩ ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፳፪ ፡ በታወጁበት ፡ ሁናቴ ፡ ከነዚህ ፡ ሰንዶች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የላቸውም ፡ በረቂቅ ፡ አውጪውም ፡ የተዘጋጁ ፡ አይደሉም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ እንደታሰበው ፡ ግላዊ ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ሕግንና ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚውልበት ፡ ጊዜ ፡ የሚመለከቱ ፡ የሕጉ ፡ ክፍሎችን ፡ አልጨመረም ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ ሕጉም ፡ በቂ ፡ አይደለም ። ቢሆንም ፡ እነዚህ ፡ ጉድለቶች ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚሟሉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። "ጠቅላላ ፡ የሆኑ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሁኔታዎች" ፡ የሚለው ፡ ሐረግ ፡ በሞዴል ፡ ውሎች ፡ በጣም ፡ ከተለመዱት ፡ ሐረጎች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ጠቅላላ ፡ ሁኔታዎች ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ችግር ፡ የሚመለከቱ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ፡ ወይም ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የመከረባቸው ፡ ሕጎች ፡ ወይም ፡ የአስተዳደር ፡ ደንቦችን ፡ በመጥቀስ ፡ ለመጨመር ፡ ይቻላል ።

14 የቸርችዎርድና ፡ የረጂና ፡ (ንግሥት) ፡ ጉዳይ ፡ (ኢንግ ፡ ፲፰፻፷፭ ፡) ሎው ፡ ሪፓርትስ ፡ ኩዊንስ ፡ ቤንች ፡ ቮል ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፻፸፫ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡

ቁጥር ፡ ፩ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፹፰ ፡ እና ፡ ከዚያም ፡ የሚቀጥሉት ፡ ገጾች ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የሚሼል ፡ መጽሐፍ ።

(ለ) በሁለት ፡ ተዋዋዮች ፡ መካከል ፡ በሚደረግ ፡ ውል ፡ አንዱ ፡ ተዋዋይ ፡ ግዴታው ፡ መፈጸሚያው ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ ሳለ ፡ ሳይፈጽም ፡ ከቀረ ፡ ሁለተኛው ፡ ተዋዋይ ፡ ግዴታውን ፡ አልፈጽምም ፡ ለማለት ፡ ያለው ፡ መብት ።

(ሸ) ያልታሰቡ ፡ ነገሮች ፡ የውሉን ፡ አፈጻጸም ፡ ሁኔታ ፡ በጣም ፡ ከለወጡት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሉን ፡ ሊያሻሽለው ፡ መቻሉን ፡ የሚገልጽ ፡ ሐሳብ ፡ ነው ። ሾን ፡ ሜሬን ፡ ዘ ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ ሲስተም ፡ (ኢንግል ፡ ውድ ፡ ክሌድስ ፡ ቲንክ ፡ ፲፱፻፶፯) ፡ ገጽ ፡ ፯፻፫—፸፬ ፡ ተመልከት ።

(ቀ) በውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ መዘግየት ፡ ኪሣራ ፡ መታሰብ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልግ ፡ አድራጐት ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፸፱—፹፰ ።

(በ) ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ ሐረግ ፡ የፈረንሳይኛው ፡ ቁጥር ፡ ፫ሺ፻፺፱(፪) ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ ሲሆን ፡ የአማርኛውና ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቁጥር ፡ ፫ሺ፻፺፱(፪) ግን ፡ የቁጥር ፡ ፫ሺ፻፺፱(፩) ፡ ሐሳብ ፡ ትንሽ ፡ በተለየ ፡ አገላለጽ ፡ በመድገም ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ በቊ ፡ ፫ሺ፻፺፱ ፡ አማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ አቅራቢዎቹ ፡ አስተዳደር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተስማሙበት ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ምንም ፡ ከጠቅላላው ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ ሁኔታዎች ፡ አልተደነገጉም ።